ምዕራፍ ሦስት - መነሐራ

- 15 -

በከባድ ውሽንፍር መካከል ብቸኛው መጠጊያ

በከባድ ውሽንፍር ፊት በፅናት መቆም ቀላል ነገር አይደለም። ውሽንፍሩ መዝነብ እንደጀመረና፣ የሙበረቅና ነጎድጓድ ብልጭታ እንደተከሠተ ወዲያውኑ ይከተላል። ጥቁሩ ዳመና ፀሐዩዋን ይተካል። ከዚያ ቀጥሎ የሚታየው የውቅያኖሱ ማዕበል ነው። አንዴ ፀጥ ብሎ ዙርያህን ይከብሃል። የሌሎች እገዛ በመፈለግ ለመጣራት እንኳን ብትሞክር መውጫ መንገድ ታጣለህ።

ወደ ባህር ዳርቻው ጠባቂ ትጣራለህ፤ ግና ምላሽ አታገኝም። ጀልባህን እንደገና ለማስተካከል ትሞክራለህ። ውጤት ታጣበታለህ። የነፍስ አድን ጀልባ ታፈላልጋለህ። እሷም ርቃ ሄዳለች። የመዋኛ ጃኬትህን ታነሳለህ። እሱም የተቀደደ ሆኖ ታገኘዋለህ። ሁሉንም አማራጭ ከተጠቀምክና ተስፋ ከቆረጥክ በኋላ በመጨረሻም ፊትህን ወደ ላይ ቀና ታደርጋለህ።

አምላክህን ትማፀናለህ!።

በዚህ ክስተት ውስጥ አንድ ለየት ያለ አስደናቂ ነገር አለ። በዚህ ክስተት ከዚህ በፊት በትክክል ተግብረህ የማታውቀውን አንድ ነገር ታስተውላለህ- የእውነተኛ ተውሒድን ምንነት ትረዳለህ። የአላህን ብቸኝነት እና አንድ አምላክነት ትገነዘባለህ። ቀድሞ በየብስ ላይ ሳለህ በሰላሙ ጊዜ ከብዙ ነገሮች ጋር እያጋራህ አላህን ታመልከው ይሆናል። እንዲረዳህም ብለህ እሱን ከሌሎች ጋር አጣምረህ ተማፅነህ ሊሆን ይችላል። አሁን ግን በዚህ ልዩ ክስተት የተነሳ ብቸኛው መጠጊያህ እሱና እሱ ብቻ ይሆናል። ሌላው ሁሉ ዝግ ይሆናል። የሚለመነው ነገር ሁሉ ይረሳና እሱ ብቻ ይዘከራል፣ ይጠራል፣ ይለመናል። እሱ ብቻ። አላህ ብቻ!!

ይህ ነው እንግዲህ ዋናው ነጥብ።

አንድ ነገር በእጅጉ በሚያስፈልገን ጊዜ ከፈጣሪ በስተቀር ሌሎች በሮች ሁሉ ዝግ የመሆናቸው ሚስጥር ምን እንደሆን ጠይቀን እናውቅ ይሆን? አዎን ብታንኳኩም አይከፈትላችሁም። ካንዱ ወደ ሌላኛው ደራሽ ትሻገራላችሁ። ሁሉም ዝግ ይሆንባችኋል። ማንኳኳት ማንኳኳት ማንኳኳት... ግን የሚከፈት በር አይኖርም። በሆነ ጊዜ ጥገኛ የነበራችሁባቸው በሮች ጭምር ሁሉ ድንገት ይዘጋሉ። ለምን? ያ ለምን ሆነ? ብለን ጠይቀን ይሆን ....

እኛ የለው ልጆች ፈጣሪያችን በሚገባ የሚያውቃቸው የተወሰኑ ልዩ ማንነቶች አሉን።ያም የማያባራ የሆነው ፈላጊነታችን ነው። ሲበዛ ፈላጊ ድሆች ነን። ደካማ ነን። እንዲሁ ችኩሎች እና ትእግስት አጥ ነን። ችግር ውስጥ ስንሆን ረዳት መፈለጋችን ተፈጥሮአዊ ባህሪያችን ነው። በዚያ መልኩ ነው የተሠራነው። ለምሳሌ - ብሩህ እና ፀሐያማ በሆነ ሰማይ፤ አየሩም ጥሩ ሆኖ እያለ የአላህን ጥበቃ የምንማፀነው ለምንድነው? አንድ ሰው የአላህን ጥበቃ የሚማፀነው መቼ ነው? ውሽንፍርና ከባድ ማዕበል ባገኘው ጊዜ መሆኑ እሙን ነው። ለዚህም ነው አላህ (ሱ.ወ.) ማዕበሉን የሚልከብን። መጠጊያ መጠለያ እንፈልግ ዘንድ በፈጠራቸው ነገሮች በኩል ይመጣብናል።

ግና ትእግስት በማጣት ባህርያችን የተነሳ ቅርብ እና ለማግኘት ቀላል ከሚመስሉን ነገሮች እርዳታን እንሻለን። ከምናየው፣ ከምንሰማውና ለመጨበጥ ቅርብ ከሆነው ነገር እርዳታና እገዛ እንማፀናለን። አቋራጩ መንገድ ስለሚመስለን ነው የምንመርጠው። ራሣችንን ጨምሮ እርዳታን አላህ ከፈጠራቸው ፍጡራን እንፈልጋለን። በጣም ቅርብ ከሚመስለን ነገር ነው የምንለምነው። የዚህች ዓለም ዱንያ ትርጉምም ይኸው ነው። ቅርብ። ዱንያ ለኛ ቅርባችንና ረዳታችን ትመስላለች። ግና አጉል ቅዠት ነው።

ከዚያ ይልቅ ለኛ ቅርብ የሆነ አለ።

እስቲ ቅርባችን ማን እንደሆነ ጥቂት እናስብ። ቢጠየቁ ብዙዎች ልባችን አልያም እኛው ራሣችን ነን ለራሳችን ቅርቦች ሊሉ ይችላሉ። ግና አላህ(ሱ.ወ.) ግን በቁርአኑ እንዲህ ይለናል፦

﴿ وَلَقَدْ خَلَقْنَا ٱلْإِنسَٰنَ وَنَعْلَمُ مَا تُوَسْوِسُ بِهِۦ نَفْسُهُۥ ۖ وَنَحْنُ أَقْرَبُ إِلَيْهِ مِنْ حَبْلِ ٱلْوَرِيدِ ﴾

«ሰውንም ነፍሱ (በሃሳቡ) የምታጫውተውን የምናውቅ ስንሆን፤ በእርግጥ ፈጠርነው፤ እኛም ከደም ጋኑ ጅማት ይበልጥ ወደርሱ ቅርብ ነን።»

(ቃፍ : 16)

በዚህ አንቀጽ ውስጥ አላህ (ሱ.ወ.) ትግላችንን እንደሚያውቅ ለኛ በማሳየት ይጀምራል። አንድ አካል የኛን ትግልና ድካም እንደሚያይ ማወቃችን ለኛ ምቾትን የሚሠጠን ነገር ነው። አላህ ነፍሣችን በምን እንደምትጠራን ያውቃል። እሱ ከራሳችንም በላይ ለኛ ቅርብ ነው። ነፍሳችን ከምትጠራብን ነገር በላይም ለኛ ቅርብ።እሱ ከደም ጅማታችንም በላይ ለኛ ቅርብ ነው።

ይህ የደም ሰር ከፍል (Jugular vein) ከሌላው በተለየ መልኩ ለምን ተጠቀሠ? ይህ የደም ቱቦ አስፈላጊውና ዋነኛው ደምን ወደ ልባችን የሚያደርሰው ነው። ይህ የደም ቱቦ የተጎዳ እንደሆነ ወዲያው የምንሞት ነው የሚሆነው። በቀላል ቋንቋ ይህ የደም

ስር ሕይወታችን ነው ማለት ነው። ነገር ግን አላህ (ሱ.ወ.) ከዚህም በላይ ለኛ ቅርብ ነው።አላህ (ሱ.ወ.) ከራሳችን ሕይወት፣ ከራሣችን በላይ፣ ከነፍሳችን በላይ ለኛ ቅርብ ነው። ደምን ወደ ልባችን ከሚያደርሰው ዋንኛ ወሣኝ ቱቦ በላይ ለኛ ቅርብ ነው።

በሌላ የቁርአን አንቀጽ አላህ ሱ.ወ. እንዲህ ይለናል ፦

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱسْتَجِيبُواْ لِلَّهِ وَلِلرَّسُولِ إِذَا دَعَاكُمْ لِمَا يُحْيِيكُمْ وَٱعْلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ يَحُولُ بَيْنَ ٱلْمَرْءِ وَقَلْبِهِۦ وَأَنَّهُۥٓ إِلَيْهِ تُحْشَرُونَ ﴾

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ!(መልዕክተኛው) ህያው ወደሚያደርጋችሁ እምነት በጠራችሁ ጊዜ፤ ለአላህና ለመልዕክተኛው ታዘዙ፤ አላህም በሰውና በልቡ መካከል የሚጋርድ መሆኑን ወደርሱም የምትሰበሰቡ መሆናችሁን እወቁ።»

(አል-አንፋል ፡ 24)

አላህ (ሱ.ወ.) ነፍስ እንዳለን ያውቃል። ልብ እንዳለንም ያውቃል። ስሜትና ፍላጎት የሚገለፁባቸው ናቸው። እነዚህ ነገሮች እንደሚፈታተኑንም ያውቃል። ነገር ግን አላህ ከነኝህ ነገሮች በላይ እንኳ ለኛ ቅርብ እንደሆነ ነገሮናል። እናም ከርሱ ስንርቅ እየሄድን ያለነው ወደ ደካማ ነገር ብቻ ሳይሆን ለኛ ቅርብ ከሆነውም እየራቅን ነው ያለነው። ሩቅ ወደሆነው ነው እየሄድን ያለነው። ጥራት እና ውዳሴ ለአላህ የተገባ ይሁን።

ይህ ተፈጥሮአችን እንደሆነ አላህ (ሱ.ወ.) ያውቃል። እሱ የሁሉ ነገር አዋቂ ነውና። ስለሆነም በማዕበል ጊዜ ሁሉንም የምንሸሸባቸውን በሮች በመዝጋት እኛን በመከላከል ወደራሱ ይመራናል። ከያንዳንዱ እኛ ልንሸሽ ካሰብንበት የውሸት በር ጀርባ መውደቅ እንዳለ እሱ በሚገባ ያውቃልና። ወደዚህ በር ብንገባ እንወድቃለን። ስለሆነም በእዝነቱ እነዚያን የውሸት በሮች ይዘጋብናል።

በእዝነቱ ማዕበል ላከና ከሱ እርዳታን እንድንለምን አደረገን። ትክክለኛውን መልስ መምረጥ እንደማናውቅ ስለሚያውቅም አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ ያለበትን የተለያዩ ምርጫዎችን አስቀመጠልንና ምረጡ አለን። ችግር በራሱ መልካም ነገር ነው። የተደገፍንባቸውን ነገሮች ሁሉ በማሳጣት፣ አማራጮቻችንን በመውሰድ ፈተናውን ቀላል ያደርግልናልና።

በከባድ ማዕበልና ውሽንፍር ፊት መቆም ቀላል ነገር አይደለም። ልናውቅ የሚገባው ትልቁ ነጥብም እሱ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) አውሎ ንፋሶችን በመላክ በጉልበታችን ወደ መሬት እንድንወርድ ያደርገናል። ለመፀለይ ትልቁ ወደሆነው የአቀራረብ አኳኋን።

- 16-

የአላህን አገዛ ከመሻት ጋር - በጀነት ውስጥ ቤታችንን መመልከት

ታሪክ ነው ተብሎ ብቻ የማይታለፍ አንድ ታሪክ አውቃለሁ። ታሪኩ የዚህን ዓለም ሳቢና አብረቅራቂ ነገር ሁሉ ንቃና ችላ ብላ በቀጣዩ ዓለም ስላለው ቤቷ ስለምትጨነቅ አንዲት ሴት የተወሳበት ነው። ራሷን በዚህ ዓለም ጊዜያዊ ጥቅም መገመት አልፈለገችም። ከወዲያኛው ዓለም ስለሚጠብቃት ከፍተኛ ሽልማት ስላሰበች በዚህ ዓለም ለሚደርስባት አሳማሚ ነገርም አልተገበረችም። ለዚያ በልቧ ለያዘችው ጥልቅ እምነቷ ለመሞት ዝግጁ ነበረች።

እሷ ንግስት ነበረች። በዚህ ዓለም ላይ አለ በሚባል ቤተመንግሥት ቅንጡ ቪላዎች ውስጥ የምትኖር ንግሥት። ግና ከቤተመንግሥቱ ባሻገር ተመለከተች። የታያት የመጨረሻው ዓለም ዋናውና እውነተኛው ቤተመንግሥት ነበር። ታላቁ መንግሥተ ሰማያት። እሱን መውረስ ነው ሀሳብና ምኞቷ። እሷም የፊርዐውን ባለቤት የሆነችው አሲያ ነበረች። ለእርሷ ይህ ፍላጎት በልቧ ውስጥ ብቻ ያለ ሀሳብ ብቻ ሳይሆን በአካላዊ እይታዋም የሚታያት ነገር ነበር። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፦

﴿ وَضَرَبَ ٱللَّهُ مَثَلًا لِّلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱمْرَأَتَ فِرْعَوْنَ إِذْ قَالَتْ رَبِّ ٱبْنِ لِى عِندَكَ بَيْتًا فِى ٱلْجَنَّةِ وَنَجِّنِى مِن فِرْعَوْنَ وَعَمَلِهِۦ وَنَجِّنِى مِنَ ٱلْقَوْمِ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴾

«ለእነዚያ ለአመኑትም የፈርዖንን ሴት አላህ ምሳሌ አደረገ። "ጌታዬ ሆይ! አንተ ዘንድ በገነት ውስጥ ለእኔ ቤትን ገንባልኝ። ከፈርዓንና ከሥራውም አድነኝ:: ከበደለኞቹ ሕዝቦችም አድነኝ" ባለች ጊዜ።» (አት-ተሕሪም ፡ 11)

የኣሲያን ታሪክ ለብዙ ጊዜ ሰምቻለሁ። በሰማሁት ቁጥር ግን ሁል ጊዜ አዲስ ይሆንብኛል። ውስጤን ይነካኛል። በቅርቡ ደግሞ ይኸው ታሪክ ከዚህ ቀደም ሰምቼው እንደማላውቀው ዓይነት ሆኖ ተሰማኝ። ይህም የኾነው በሆነ ምክንያት ነበር። ከጥቂት ወራት በፊት ከባድ ፈተና ገጥሞኝ ነበር። በሕይወታችን መልካም እና የመልአክ የመሠለች ነፍስ ያላቸው ጓደኞችን ማግኘት በዋጋ ሊተመን የማይችል ትልቅ ውበት ነው። ዛሬ በችግር ላይ ስትወድቅ አንዲት የጽሑፍ መልዕክት መላክ፣ ወይም ደግሞ ፌስቡክን በመጠቀም ያለህበትን ሁኔታ መግለጽ፣ ወይም ደግሞ የልብህ ጓደኞች ለሆኑት አንዲት መስመር የኢሜይል መልዕክት መላክ ብቻ በቂ ነው። ይህ በራሱ ትልቅ የአላህ ፀጋ ነው። በዚህን ጊዜ ወዲያውኑ እጅግ የበዙ፣ ውብ የሆኑ ነፍሶች ዱዓ ሲያረጉልህ፣ መልካም ነገርን ሁሉ

ሊመኙልህ ታያለህ። ሱብሓነላህ!። ለአላህ ውዳሴና ጥራት ይገባው።

እና እኔም ከወዳጆቼ ዱዓ ነበር የጠየቅኩት። አንድ ሰው ለሌላው ወንድም እህቱ ሊሠጥ ሚችለውን ትልቁን ስጦታ ነበር የጠየቅኩት። ልባዊ የሆነ ዱዓ እንዲያደርጉልኝ ነበር የጠየቅኩት። ግና ያገኘሁት ምላሽ ከጠበቅኩት በላይ እጅጉን አስደመመኝ። ያንን ትልቅ የአላህ ስጦታ ፈጽሞ ልረሳው አልችልም። ካዕባ ፊት ቆመው ጭምር ሌሊት ላይ ዱዓ ያደረጉልኝን ሰዎች አገኘሁ። ጉዞ ላይ እያሉ፤ ልጅ በተወለደላቸው ቅጽበት ጭምር ዱዓ ያደረጉልኝ ነበሩ። ከብዙ ሰዎች በኩል እጅግ በርካታ ዱዓ ደረሠኝ። ከሁሉም በላይ አንድ እጅግ የነካኝና ፈጽሞ የማልረሳው ዱዓ ነበር። ዱዓው በቀላል የቴክስት ሚሴጅ (የሞባይል ጽሑፍ መልዕክት) የተላከልኝ ሲሆን እንዲህ ይነበባል ፦

"ሁሉም መከራ ቀላል ሆኖ ይታይሽ ዘንድ አላህ የጀነት ውስጥ ቤትሽን ያሳይሽ!" ባነበብኩበት ቅጽበት ይህ መልዕክት እጅጉን ነካኝ። ውስጤ ድረስ ሰርስሮ ዘለቀኝ።በዚህን ጊዜ ወዲያው ነበር የአሲያ ታሪክ ትዝ ያለኝ። በቅጽበትም እጅግ የሚገርም ነገር ተገነዘብኩ። አሲያ አንድ ሰው ፈጽሞ ሊቋቋመውና ሊያስበው በማይችል የቅጣት ስቃይ ውስጥ አልፋለች። ፈርዖን በዚህ ምድር ላይ ከኖሩ ጨቋኝ አምባገነኖች ሁሉ ግንባር ቀደሙ ነው። የግብፅ አገረ ገዢ የነበረው ፈርዐውን ያኔ በጊዜው ለንግሥት አሲያ መሪዋ ብቻ አልነበረም፣ ባሏም ጭምር ነበር። በድፍረት እኔ ታላቁ ጌታችሁ ነኝ ያለ እቡይ ነበር -ፈርዐውን። ባለቤቱ አሲያ በአላህ ማመኗን በሰማ ጊዜ ቅጣቱን አበረታባት። ከእምነቷ እስከትመለስ ድረስም ማሰቃየቱን ቀጠለ። ከስቃዩ የተነሳ ልትሞት መጨረሻ አካባቢ አሰቃቂ ቅጣቱን በመቀበል ላይ እያለች ድንገት ፈገግ አለች። የሰው ልጅ ሊቋቋመው በማይችለው ስቃይ መሐል ሆና ነበር ፈገግ ያለችው - አሲያ።

ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? በአሰቃቂ ቅጣት ላይ እያለ አንድ ሰው እንዴት ፈገግ ሊል ይችላል? በጉዞ ላይ የመኪና መንገድ መዘጋጋት ሲያጋጥመን፤ ወይም አንድ ሰው የተሳሳተ መንገድ ሲያሳየን ንዴቱን መቋቋም እንችላለን?

ነቢዩ ኢብራሂም (ዐ.ሰ.) በሰው ልጅ ታሪክ እጅግ ትልቅ በሆነው ከባድ መከራ ውስጥ ወድቀው፤ እሳት መሃል ሆነው ቅዝቃዜና ሰላም እንዴት ሊሠማቸው ቻለ? ለምንድነው አንዳንድ ሰዎች ብዙ መከራና ስቃይ ገጥሟቸው ሳሉ ምንም ብሶት ሲሰሙ የማይታዩት? አንዳንዶች ደግሞ ምንም ነገር ሳይሆኑ ብሶት የሚያበዙት ለምንድነው? አንዳንዶቻችን በትልቅ ችግር ውስጥ ወድቀን ትዕግስታችን የሚበዛው ለምንድነው? ሌሎቻችንስ ትንሽ ችግር አግኝቶን ትዕግስት የምናጣበት ምክንያት ምንድነው?

ስቃይና መከራን የምናሰማው አንዳንድ ጊዜ ነገሮች ከመቋቋም አቅማችን በላይ ስለሆኑ ይመስለኝ ነበር። ከችግር ጋር በተያያዘ ችግሮች በህመም ደረጃቸው የሚቀመጡ ሁላ

ይመስለኝ ነበር። ለምሳሌ አጅግ የምንወደው ሰው ሲሞትብን በትራፊክ ጥሰት ከመቀጣት የበለጠ ለመቋቋም የሚከብድ ሀመም ነው የሚሰማን። ይህ በርግጥም ግልፅ ነገር ነው። አዎን በጣም እውነት ይመስላል።